**በአፋጣኝ የሚለቀቅ**

አድራሻ፡- Cynthia Santana/የኮሙኒኬሽን ስራ አስኪያጅ
206-256-5219
cynthia.santana@seattle.gov

# Office of Labor Standards የ 2023 የዝቅተኛ መነሻ ደመዎዝ መጠንን አስታወቀ

**Seattle, WA** – (ኦክቶበር 4፣ 2022) – የሲያትል Office of Labor Standards (OLS፣ የስራ መደብ መስፈርቶች ቢሮ) ከጃንዋሪ 1/2023 ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ የሲያትል የመነሻ ደመዎዝ መጠን ላይ ጭማሪ መደረጉን አስታወቀ። ዓመታዊ የአነስተኛ ደመዎዝ ጭማሪ በ Minimum Wage Ordinance (መነሻ የደመወዝ መጠን) መሰረት የተደረገ ነው። የመነሻ ደመወዙ የሰራተናውን የስደተኝነት ሁኔታ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ተፈጻሚ ይሆናል። የዝቅተኛ መነሻ ደመዎዙ ለ Seattle Tacoma Bremerton በ Consumer Price Index (CPI፣ የተጠቃሚ ዋጋ አመልካች) መሰረ+ት የዋጋ ግሽፈቱን ተመን የሚያንጸባርቅ ነው።

- **ለግዙፍ ቀጣሪዎች** (501 ወይም ከዚያ ለሚበልጡ ሰራተኞች) **የ 2023 የመነሻ ደመዎዝ መጠን $18.69/በሰዓት ነው።**
- ለሰራተኛው የሕክምና ጥቅማ ጥቅም ቢያንስ **$2.19/በሰዓት** ለማያዋጡ እና/ወይም ሰራተኛው ቢያንስ **$2.19/በሰዓት** ጉርሻ ለማያገኝባቸው **አነስተኛ ቀጣሪዎች** (500 ወይም ከዚያ ለሚያንሱ ሰራተኞች) **የ 2023 የመነሻ ደመዎዝ መጠን $18.69/ሰዓ**ት ነው።
- ለሰራተኛው የሕክምና ጥቅማ ጥቅም ቢያንስ **$2.19/በሰዓት** ለሚያዋጡ እና/ወይም ሰራተኛው ቢያንስ **$2.19/በሰዓት** ጉርሻ ለሚያገኝባቸው **አነስተኛ ቀጣሪዎች የ 2023 የመነሻ ደመዎዝ መጠን $16.50/በሰዓት** ነው።

Minimum Wage Ordinance በከተማ ውሱኖች ውስጥ ለሚሰሩ ሰራተኞች ዝቅተኛውን የደውወዝ መጠን ይወስናል። የሲያትል ወቅታዊ ዝቅተኛ የደውወዝ መጠን ለግዙፍ ቀጣሪዎች እና ቢያንስ $1.52/በሰዓት ወደ ሰራተኛው የሕክምና ጥቅማ ጥቅሞች ለማይከፍሉ እና/ወይም ሰራተኛው በጉርሻ መልክ $1.52/በሰዓት ለማያገኙባቸው አነስተና ቀጣሪዎች $17.27/በሰዓት ነው። ለሕክምና ጥቅማ ጥቅሞች $1.52/በሰዓት የሚከፍሉ እና/ወይም ሰራተኛው ቢያንስ $1.52/በሰዓት በጉርሻ የሚያገኝባቸው አነስተኛ ቀጣሪዎች አሁን ላይ $15.75/በሰዓት ይከፍላሉ።

OLS የ 2023 የስራ ደረጃዎችን የተመለከቱ መረጃዎችን የያዘ የተሻሻለ የስራ ቦታ ፖስተር ለሁሉም በ Seattle የንግድ ፈቃድ ለሚሰሩ አካላት ይልካል። ስራ ቦታ ፖስተር ኮፒዎች (በእንግሊዝኛ) ከ OLS ድረገጽ እዚህ ጋር በአሁኑ ሰዓት ለማውረድ ይገኛሉ። ወደ 25 ሌሎች ቋንቋዎች የተተረጎሙ ፖስተሮች በ OLS ቋንቋዎች ድረገጽ ላይ ኦንላይን ይገኛሉ።

በ Seattle የሰራተኛ ደረጃዎች ላይ የቅርብ ጊዜ ዝማኔዎችን ለማግኘት ለ OLS ጋዜጣ በ OLS ድረገፅ ላይ ይመዝገቡ።

- **እርዳታ ለአሰሪዎች፦** የ Seattle የመነሻ ደመዎዝ እና ሌሎች የስራ ደረጃዎችን በማክበር ረገድ ነጻና ግላዊ እገዛ ለማግኘት፣ ወደ 206-256-5297 ይደውሉ፣ በ business.laborstandards@seattle.gov ወይም እዚህ ጠቅ አድርገው ኦንላይን የመጠየቂያ ቅጽ ይሙሉ።

- **እርዳታ ለሰራተኞችና ለሕዝቡ፦** ጥያቄ ለመጠየቅ፣ ቅሬታ ለማቅረብ ወይም መረጃ ለመስጠት፣ በስልክ ቁጥር 206-256-5297 ይደውሉ፣ በ workers.laborstandards@seattle.gov ኢሜይል ይላኩ፣ ወይም የድረገጽ ቅጽ ለመሙላት እዚህ ላይ ጠቅ ያድርጉ።

####